በስደት ላይ ያለው ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጽ/ቤት

THE LEGITIMATE HOLY SYNOD OF THE ETHIOPIAN ORTHODOX TEWAHEDO CHURCH MAIN OFFICE IN EXILE

Date:-01/25/2018
Ref. No:03/01/2018

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን፤

“እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ የዋይታና የመራራ ልቅሶ ድምፅ በራማ ተሰማ፤ ራሔል ስለ ልጆችዋ አለቀሰች፤ የሉምና ስለ ልጆችዋ መጽናናትን እንቢ አለች።”ኤር31፡15

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከሚመራው በስደት ላይ ከሚገኘው ከሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በሀገራችን ኢትዮጵያና በሕዝባችን ላይ አሸባሪው ወያኔ እያደረሰ ያለውን ገደብ የለሽ የዘር ማጥፋት ዘመቻ አስመልክቶ የወጣ መግለጫ፤

ሀገራችን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በተለያዩ የውጭ ወራሪ ኃይሎችና በተለይም በፋሽሽት ጣልያን ወረራ የደረሰባቸው ከባድ የመከራ ዓመታት፡ አሁን በዘረኛው የወያኔ አረመኔያዊ አገዛዝ እየደረሰባቸው ካለው ግፍ ጋር ሲነፃፀር የአሁኑ የወያኔ አረመኔያዊ የጭቆና አገዛዝ ከሁሉም እጅግ የባሰና የከፋ ተወዳዳሪም ያልተገኘለት በዚህ ጊዜ ይረሳል የማይባል የታሪክ ጠባሳና ከባድ ቁስል መሆኑ ለሁላችንም ግልጽ ነው።

ጥንታዊትና ታሪካዊት የሆነችው ሀገራችን ኢትዮጵያ ለዘመናት ታፍራና ተከብራ፡ የውጭ ጠላትንም አሳፍራ ሕያው ታሪክን በማስመዝገብ በዓለም የታወቀች የጀግኖች ሀገር መሆንዋን ታሪክ የሚመሰክረው እውነት ነው። አሁን ግን በኢትዮጵያዊነት ስም የኢትዮጵያዊነት መልክ እንጂ፡ የኢትዮጵያዊነት ሞራል ስሜትና ባሕርይ በሌላቸው የሀገራችንን ታሪክና ሕዝባችንንም አጥፍተው ለመጥፋት በተቀጠሩ ባንዳዎች ሀገራችን በጥፋት፡ ሕዝባችንም በሞት የገደል አፋፍ ላይ ይገኛሉ።

ዘረኛው ወያኔ የሀገራችንን ጥንታዊ የታሪክ ገጽታ በመቀየር፡ ታላቂቱን ሀገራችንን ያለወደብ በማስቀረት ለብዙ ሽህ ዓመታት ተስማምቶና ተከባብሮ የኖረውን ሕዝባችንን በዘር፤ በቋንቋና በሃይማኖት በመከፋፈል እየፈጸመ ያለው ታሪካዊ በደል አልበቃ ብሎት፡ እናቶችን በእስር ቤት በማጎር፡ ሕፃናትን ያለአሳዳጊ በማስቀረት፡ መተኪያ የሌላቸውን የሀገርና የወገን ጠበቃ የሆኑትን ምሁራን በጨለማ እስር ቤት በማፈንና በልዩ ልዩ ስቃይ በማሰቃየት፡ ሀገር ተረካቢውን ተተኪ ትውልድ ለነገ እንዳያስብ በፍርሃትና በጭንቀት በማሰቃየት የሀገራችንን ክብርና ሉዓላዊነት ገፎ መሬትዋንም ለርካሽ የፖለቲካ ተግባር ለባዕዳን በመሸጥ እየፈጸመ ያለውን በደል እንደ እድገትና ሥልጣኔ በመቁጠር የጥፋት አላማውን በመፈጸም ላይ ይገኛል። በመሆኑም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ በብሔራዊ ደረጃ የሚከበረውን የጥምቀትን ክብረ በዓል ለማክበር በወልድያ እና በአካባቢው ታቦታቱን (ታቦተ ሕጉን) ይዘው ሥርዓተ አምልኮ በሚያከናውኑ ካህናትና

ምእመናን ላይ የአስለቃሽ ጋዝ ጢስ በመተኮስ፡ ካህናቱ በአስለቃሽ የጋዝ ጢስ ታፍነው እንዲወድቁ በማድረግ ክብረ በዓሉን በማድናቀፍና በክብረ በዓሉ ቦታ በሚገኙ ንጹሀን ዜጎች ላይ እና እንዲሁም በመላ የሀገራችን ክፍሎች በሚገኙ ወገኖቻችን ላይ ዘረኛው ወያኔ የምድር ተሽከርካሪዎችንና የአየር ላይ በራሪዎችን በመጠቀም በዘመናዊ መሣሪያ እየፈጸመ ያለውን የጅምላ ጭፍጨፋና ግድያ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራው በስደት ላይ የሚገኘው ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በጥብቅ እያወገዘ፤ ለኢትዮጵያውያን ሁሉ የሚከተለውን የአደራ ጥሪ ያስተላልፋል።

1. ሳይበድሉ በዘረኛው ወያኔ በግፍ ለተገደሉት በመላ የሀገራችን ክፍሎች ለሚገኙ ወገኖቻችን በየአብያተ ክርስቲያናቱ ጸሎተ ፍትሐት እንዲደረግላቸው ቅዱስ ሲኖዶስ ወስኖአል።
2. ቤተሰቦቻቸው ለተገደሉባቸውና በመሪር ኃዘን ላይ ለሚገኙ ወገኖቻችን ቅዱስ ሲኖዶስ ጥልቅ ኃዘን የተሰማው መሆኑን እየገለጸ፡ እግዚአብሔር አምላካችን አጽናኝ በሆነው በቅዱስ መንፈሱ እንዲያጽናናቸው የዘውትር ጸሎቱ ነው።።
3. ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉ እና በልዩ ልዩ ችግር ለሚገኙ ወገኖቻችን፡ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በያላችሁበት አስፈላጊውን እርዳታ እንድታደርጉላቸው ቅዱስ ሲኖዶስ የአደራ ጥሪውን ያስተላልፋል።
4. ለሀገር መከላከያ ሠራዊትና ለፖሊስ አባላት የቀረበ ጥሪ፤ በዓለም ታሪክ እንደሚታወቀው ሁሉ የሀገር መከላከያ ሠራዊትና የፖሊስ አባላት፡ የሀገር ዳር ደንበር በውጭ ወራሪ ኃይል እንዳይደፈር የሀገሩን ዳር ደንበር ያስከብራል፡ የዜጎቹንም ደኅንነት ይጠብቃል እንጂ በራሱ ወገን ላይ የጅምላ ጭፍጨፋ ግድያ አይፈጽምም፤ ስለሆነም በዚህ ፈታኝ ወቅት፡ ጊዜ ከሚለውጠው ሐላፊና ጠፊ አገዛዝ የጅምላ ጭፍጨፋ ግድያ ትእዛዝና መመሪያ በመቀበል ነገ መጠለያ የሚሆናችሁን ወገናችሁን ከመግደል እንድትቆጠቡ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ በእግዚአብሔር ስም ይጠይቃል።
5. ለሀገራችን ከብር ለወገኖቻችን ሕይወት በመቆርቆር በተለያየ የፖለቲካ ድርጅት ስም ራሳችሁን የምትጠሩ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎችና አባላት፡ በዚህ እጅግ በጣም ፈታኝ በሆነ ወቅት የግል ሐሣባችሁን ወደ ጎን በመተውና በመቻቻል በአንድ ሐሣብ ተስማምታችሁ ለሀገራችን ሉዓላዊነት እና ለሕዝባችን ድኅንነት፡ ከሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ጎን በመሰለፍ ሀገራችንን ከጥፋት ሕዝባችንንም ከሞት እንድናድን ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ በእየቀኑ እየተገደለ በሚገኘው ሕዝባችን ስም ይጠይቃል።
6. የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! ለዘመናት መታወቂያህ ሁኖ የኖረውን ፍጹም ጨዋነትህንና ሰላም ወዳድነትህን ለዓለም አሳይተሃል፤ የአንተን የልብ ትርታ በማዳመጥ በሰላማዊ መንገድ አንተን ወክለው የዘረኛውን የወያኔን የጭቆና አገዛዝ በመቃወማቸው እራሳቸውን ለእስራት፡ ለስቃይና ለውርደት፡ ውድ ሕይወታቸውንም ሳይቀር ለሞት አሳልፈው ለሰጡ ለኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች የዘመናችን ሰማእታት መባል ይገባቸዋል።

Address: 15521 Orchard Run Drive, Bowie, MD20715, Tel: 403-266-1178, Email:abunemichael@live.ca
Mailing address: 2515 Edmonton Trial NE, Calgary, Alberta, Canada T2E 3M9

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! የከሀዲውን የወያኔን ልዩ ልዩ ጸዋትወ መከራ የምትሸከምበት ትከሻና አቅም የለህም፤ ጥበብህና እውቀትህ፡ ጋሻህና መከታህ፡ ኃይልህና አዳኝህ ሁሉን ለማድረግ ሥልጣን ያለው አምላክህ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ስለሆነም አምላክህ እግዚአብሔርን በፍጹም ነፍስህ፡ በፍጹም አሳብህ፡ በፍጹም ልብህ፡ በፍጹም ኃይልህ ውደደው፤ በዘር፡ በቋንቋና በሀይማኖት ሳትለያይ በህብረትና በአንድነት ሁነህ ወደ እርሱ ብቻ ዘወትር ጸልይና ተማጸን፤ ሁሉን ማድረግ የሚቻለውን አምላክህን እውነተኛ መሪ አድርገህ በእምነትህ እና በአንድነትህ ጽና። በእምላክህም ስም እንደ እውነተኞቹ አባቶችህ “እክህደከ ሰይጣን ወያኔ” ብለህ ወያኔን ክጄሃለሁ በለው፤ እንዲህ ያደረክ እንደሆነ አምላክህ እግዚአብሔር ከከሀዲው የወያኔ አረመኔያዊ አገዛዝ ነጻ ያወጣሀል። የኢትዮጵያ አምላክ የጨለማውን አገዛዝ እድሜውን እንዲያሳጥረው፡ ለሀገራችንም ቅን መሪን እንዲተካ ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ በዘውትር ጸሎቱ ያስብሃል።

ልዑል እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይጠብቅ! ሕዝባችንንም ይባርክ!

Aba Michael
Arcbishop
vice secretary of the Holy Synod
አባ ሚካኤል
ሊቀ ጳጳስ የቅዱስ ሲኖዶስ ም/ዋና ጸሐፊ